የሰ/መ/ቁ.128153

ሐምሌ 27 ቀን 2009ዓ/ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ

ቀነዓ ቂጣታ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- የደቡብ ወሎ ዞን የኩታበር ወረዳ 01 ቀ/አስተ/ጽ/ቤት ዐ/ሕግ ዩሐንስ ተገኝ- ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1ኛ ወ/ሮ ጡርዬ አሊ
2ኛ አቶ ካሣየ ኃይሉ
አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው የአሁን ተጠሪዎች በስር የአብክመ ደሴ ወረዳ ፍ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/67 ያልተወረሰ ቤት ይመለስልኝ በማለት ባቀረቡት ክስ መነሻት ፍርድ ቤቱ ክርክር ያስነሳው የቤት ቁጥር 407 አዋጅ ቁጥር 47/67 የተወረሰ አይደለም ብሎ በሰጠው ውሳኔ እና ይግባኝ ሰሚውም ሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም በማለት በመወሰናቸው መነሻነት በስር ፍርድ ቤቶች የተፈጸመ የህግ ስህተት በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በሚል የአሁን አመልካች ባቀረበው አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡

የስር ከሳሽ የነበሩት የአሁን ተጠሪዎች ሲሆኑ የክሱ ይዘትም በኩታበር ወረዳ ቀበሌ 01 ውስጥ የስር 1ኛ ተከሳሽ አባት ከ2ኛ ተከሳሽ በዚህ የሰበር አቤቱታ ያልተካተቱ ወ/ሮ አይናዲስ እሬታ ከተባሉት ጋር በጋብቻ ሲኖር የቤት ቁጥር 407 የሆነውን 2 ክፍል ቤት መስራታቸውን በ1977ዓ/ም አባታቸው በሞት ሲለዩ 1ኛ ተከሳሽ ቤቱ በአዋጅ የተወረሰ በማስመሰል ለ2ኛ ተከሳሽ ማከራየቱን ቤቱን እንዲለቁ ቢጠየቁም ፈቃደኛ ያለመሆናቸውን በመግለጽ ክርክር የተነሳበት ቤት በአዋጅ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ቁ.47/67 የተወረሰ ባለመሆኑ ለቀው እንዲያስረክቧቸው እንዲወሰንላቸው ክስ ማቅረባቸውን ያመለክታል፡፡

የስር 1ኛ ተከሳሽ/ የአሁን አመልካች/ ባቀረበው መቃወሚያ ቤቱ ከ1972ዓ/ም ጀምሮ የተወረሰ መሆኑን በቤቱ ላይ ከሳሾች መብት እና ጥቅም የሌላቸው በመሆኑ ክስ የማቅረብ መብት አይኖራቸውም ክሱም የቀረበው ከ30ዓ/መት በኃላ በመሆኑ በይርጋ ይታገዳል ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የለውም ከሳሾች ቀድመው በሚመለከተው አካል ሳያስወስኑ በፍርድ ቤት ክስ አቅርበው ሊስተናገዱ አይገባም በማለት ክሱ ውድቅ እንዲሆንለት በመጠየቅ ተቃሟል፡፡

በዚህ መቃወሚያ መነሻነትም ጉዳዩን የመረመረው ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት  ስልጣን የለኝም በማለት የወሰነ መሆኑን እና እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ደሴ አካባቢ ቋሚ ችሎት በይግባኝ ክርክር ተደርጎበት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር  የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ አከራካሪው ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/67 የተወረሰ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ የግራ ቀኙን ማስረጃዎች ሰምቶና መርምሮ ቤቱ የተወረሰ ለመሆኑ ሊያስረዳ የሚችለል ዋና ቅጹ እንዲቀርብ አድርጎ መዝኖ የመሰለው ውሳኔ እንዲሰጥ በሰጠው ውሳኔ መሰረት ቤቱ የተወረሰ ስለመሆኑ የሚገልጽ ዋናውን ኮፒ እንዲያቀርቡ የግራ ቀኙን ማስረጃዎች ትዕዛዝ መስጠቱን የቀረበው የሰነድ ማስረጃ ቅጽ 003 በጦርነትና በተለያየ ምክንያት በመጥፋታቸው በርካታ የይገባኛል ጥያቄዎችን ማስነሳቱን ይህን ችግር ለመቅረፍ መረጃዎችን አደራጅቶ ለመያዝ ሲባል በአብክመ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ በአዋጅ ቁጥር 47/67 የተወረሱ ቤቶች ወቅታዊና ገላጭ ማስረጃ ቦታው ድረስ በመሄድ በቀበሌ ወይም በኪቢአድ እና በሥራና ከተማ ልማት መመሪያ የተሞሉ ቅጽ 001 እና 002 በመረጃነት እያገለገሉ መሆኑ ስለሚታወቅ በዚህ መሰረት በሟች ሀይሌ ....... ስም የተገኘ ይህንኑ መረጃ በቁጥር ቤ/መ/ል/116/07 በቀን 28/08/02 ዓ/ም መላኩን በድጋሚ ያንን ማስረጃ እንድንልክ ፍርድ ቤቱ ያዘዘ ቢሆንም ቀድሞ ከቀረበው ማስረጃ ሌላ ማቅረብ እንደማይችል ገልጿል፡፡

ቀድሞ ቀርቦ የነበረው ማስረጃ ደግሞ ቅጽ 001 እና 002 ሲሆን ይህ ደግሞ ቤቱ መቼ እንደተወረሰ የማያሳይ በመሆኑ ቅፁን የሞሉትን ሰዎች ፍርድ ቤቱ አስቀርቦ መስማቱን 3 ምስክሮች ባልተለያየ ቃል ቅጹ የተሞላው በ1989ዓ/ም መሆኑን ቅፁን ሊሞሉ የቻሉበትም ከዞን ከተማ ልማት መጥተው ቀበሌው ኪራይ የሚቀበልባቸውንና የሚያስተዳድራቸው የሚል መዝገብ ቀርቦላቸው በዛ መሰረት የሞሉ መሆኑን እንጂ በአዋጁ መወረስ ያለመወረሳቸውን የማያውቁ መሆኑን መመስከራቸውም በግራ ቀኙ የቀረቡ ምስክሮችንም ሰምቶ የቀረበው ቅጽ በአዋጅ የተወረሱ ቤቶች መሆናቸው ተረጋግጦ የተሞላ ሳይሆን በትዕዛዝ የተሞላ መሆኑን ተረድቻለሁ በመሆኑም ክርክር የቀረበበት ቤት በአዋጅ የተወረሰ አይደለም፣ በሕጋዊ መንገድ ስለመያዙም ማረጋገጥ አልተቻለም በመሆኑም ተከሳሽ ለከሳሽ ቤቱን ያስረክብ ሲል መወሰኑን የፍርድ ቤቱ ውሳኔ ያሳያል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አመልካች በስር ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ ይግባኝ ቢልም ይግባኙን ያየው የአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የደሴ አካባቢ ቋሚ ችሎት በትእዛዝ ይግኙን ውድቅ አድርጎታል፡፡ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታም ቢያቀርብ የሰበር አጣሪ ችሎቱ በአብላጫ ድምጽ አያስቀርብም ብሎ አቤቱታውን ውድቅ ማድረጉን የውሳኔው ግልባጭ ያመለክታል፡፡

አመልካች በስር ፍርድ ቤቶች በተሰጠው ውሳኔ ላይ መሠረታዎ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ ሲል ግንቦት 03 ቀን 2008ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡

የአቤቱታው ይዘትም በአጭሩ፣ ክርክር የተነሳበት ቤት ለረዠም ጊዜ በመንግሥት እጅ ተይዞ የሚገኝ ሆኖ እያላ እና ተጠሪዎች ማስረጃ ሳያቀርቡ ቤት ይመለስልን ብለው ሊጠይቁ አይገባም፡፡ በተመሣሣይ ጉዳይ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሕግ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡ ቅጽ 001 እና 002 ተሞልቷል፣ አውራሻቸው ቤቱን አስወርሰው አበል እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል፣ አስተዳደሩም ቤቱን እያከራየ ገንዘብ ይቀበል እንደነበረም ማስረጃ አቅርበናል፡፡ በመሆኑም በአዋጅ የተወረሰ ቤትን የማከራከር የፍርድ ቤት ሥልጣን እንዳልሆነ እየታወቀ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአዋጅ ተወርሷል ወይንስ አልተወረሰም ሚለውን የማየት ሥልጣን የፍርድ ቤት ነው ሲል መመለሱ ስህተት ነው ይባልልን፣ በስር ያነሳው የይርጋ ጥያቄ ሳይወሰን ማለፉ ስህተት ነው ይባልልን፣ ቅጽ 003 በጦርነት እና በተለያየ ምክንያት ሊገኝ ባይችልም የቀረቡት ቅጽ 001 እና 002 ሌሎች ቤቱ የተወረሰ መሆኑን የሚያሳዩ ሌሎች አመልካች ማስረጃዎችን አቅርበን እያለ በአዋጅ ቤቱ አልተወረሰም ተብሎ የተሰጠው ውሰሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል ሲል አቤቱታውን አቅርቧል፡፡

አቤቱታውን የመረመረው የሰበር አጣሪ ችሎትም የስር ፍርድ ቤት ቅጽ 001 ብቻ መሠረታ በማድረግ ሌሎች ማስረጃዎችን አልፊው የመወሰናቸውን አግባብነት ለመመርመር ሲባል አቤቱታው ለሰበር ችሎት ይቅረብ ሲል በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት መዝገቡ ሊቀርብ ችሏል፡፡

አቤቱታው ከማስቀረቢያ ነጥቡ ጋር ለተጠሪዎች እንዲደርሳቸው ተደርጎ የካቲት 30 ቀን 2009 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ መልሱ በአጭሩ እንደሚያመለክተው በስር ፍርድ ቤት ክርክሩ ያስነሳው ቤት በአዋጅ ያልተወረሰ መሆኑን ማስረጃ አቅርበን ፍሬ ነገር ለማጣራት ስልጣን የተሰጠው ፍርድ ቤት ቤቱ ያለመወረሱን አረጋግጧል፡፡ የፌደራልም ሆነ የክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያልተሰጣቸው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ነገር ግን አጣሪ ችሎቱ ከያዘው ጭብጥ አኳያም ቢሆን አመልካቸ ክርክር ያስነሳው ቤት በአዋጅ ስለመወረሱ የሚያረጋግጥ ማስረጃ አላቀረበም፡፡ ነበሩ የተባሉትም ማስረጃዎች በጦርነት ወድመው ሊሆን ይችላል ለተባለው በአመልካች ምስክሮች የወደመ ነገር እንደሌላ አረጋግጠዋል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካች በጊዜው ቤቱ መወረሱን ማረጋገጥ የሚጠበቅበት በቅጽ 001 እና 003 እንጂ በሌላ ሊሆኝ እችልም በለት በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ የህግ ስህተት ስለሌለ እንዲጸናላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም የመልስ መልሱን አቅርቦ አያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን እኛም የቀረበውን አቤቱታ እና አጠቃላይ ጉዳዩን አግባብነት ካለው የህግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነ ድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እ ንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አመልካች ክርክር ያስነሳውን ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/67 ወርሽ ለረዠም ጊዜ ሳከራይ ቆይቻለሁ በመሆኑም ማስረጃዩ በጦርነት እና በተለያዩ ምክንያቶች ወድመውብኛል በመሆኑም ከክልሉ ከተማ ልማት በተሰጠው መመሪ መሰረት ማስረጃዎችን እንደገና አደራጅቻለሁ የቤት ቁጥር 407 የሆነውም ቤት መወረሱን በማስረጃ አስረድቸ እያለ ቅጽ 003 አልቀረበም በማለት በስር ፍርድ ቤት ቤት በአዋጅ አልተወረሰም ሲል  የሰጠው ውሳኔ ስህተት ነው ይባልልኝ በማለት እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡ የስር ፍርድ ቤት በቅድሚያ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን የዘጋው ቢሆንም በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ክርክር ያስነሳውን ቤት በአዋጅ መወረስ አለመወረሱን የማጣራት ስልጣን የፍርድ ቤት ነው በሚል ቅጽ 003 ዋናው  እንዲቀርብ በማድረግና አጠቃላይ ማስረጃውን በመመዘን ውሳኔ እንዲሰጥ በመለሰለት መሰረት ቅጽ 003 አመልች እንዲያቀርብ የጠየቀ መሆኑን አመልካች ግን ከላይ በተገለጸው  መልኩ ቅጽ 003 ሊያገኝ ያልቻለ እና እሱን ይተካሉ ያላቸውን ቅጽ 001 እና 002 እንዲሁም ሌሎች ደጋፊ ማስረጃዎችን ማቅረቡን  ፍርድ ቤቱም ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ቅጽ 001 እና 002 የሞሉትን ሰራተኞች አስቀርቦ በምስክርነት ማስማቱን እና  በሰጡት ምስክርነትም ከመዝገብ ላይ መገልበጣቸውን እንጂ ስለመወረስ አለመወረሱ የማያውቁ መሆኑን መስክረዋል፡፡

በፍሬ ነገር ደረጃ ማስረጃን የማጣራትና የመመዘን ሥልጣን ያለው የስር ፍርድ ቤት ከላይ በተገለጸው መልኩ ማስረጃውን ያጣራና ውሳኔም የሰጠ ሲሆን ከዛ በዘለለም አመልካች ራሱ በስር ፍርድ ቤት በተከራከረ ጊዜ በ1972ዓ/ም ቤቱን መውረሱን እና መከራየቱን ገልጿል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 47/67 ደግሞ ትርፍ ቤቶች የተወረሱት በ1967ዓ/ም በመሆኑ በአዋጁ ይህ ክርክር ያስነሳው የተወረሰ መሆኑን የሚያሳይ አይደለም፡፡

በዚህ አልፎም ቢሆን በአዋጅ 47/67 የተወረሰው ትርፍ ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪዎች ትርፍ ቤት እያላቸው ይህን ቤት ይመለስልኝ ብለው ስለመጠየቃቸው የሚያሳይ ክርክርም በስር ፍርድ ቤት አልቀረበም፡፡

በአጠቃላይ አመልካች በሰበር ታይቶ እንዲታረምለት የጠየቀው ጉዳይ በአግባቡ ማስረጃ ሳይመዘንልኝ ቀርቷል በማለት ሲሆን በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ እንደተመለከተው ግን ከይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አስቀርበህ መዝነህ ውሳኔ ስጥ በሚል በተሰጠው መመሪያ መሰረት በአግባቡ ማስረጃውን መዝኖ ውሳኔ መስጠቱን የተረዳን በመሆኑ በዚህ ረገድ የስር ፍርድ ቤት የፈፀመው መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለ መሆኑን እና ይግባኝ ሰሚውም ሆነ ሰበር ሰሚ ችሎቱ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ማጽናታቸው የሚነቀፍበት የሕግ መሰረት አላገኘንም፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

1. የደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ቡታበር ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.0115398 በ10/6/2008ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ የአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የደሴ አካባቢ ቋሚ ችሎት በመ/ቁ.25054 በ15/7/2008ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ እና የአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት በመ/ቁ.0313923 በ10/08/2008ዓ/ም በዋለው ችሎት በአብላጫ ድምጽ የሰጠው ትዕዛዝ የተፈፀመበት መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የውሳኔው ትክክል ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይድረስ፡፡
3. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለወጣ ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም